አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ
BIIROO BARNOOTA BULCHINSA MAGAALAA FINFINNEE
ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION EDUCATION BUREAU







# የ2016 ትምህርት ዘመንን አፈፃፀም ውጤታማ ለማድረግ

# **በ2015 ትምህርት ዘመን የነበሩትን ጥንካሬና ድክመት እንዲሁም በ2016 ትምህርት ዘመን ልንከተላቸው የሚገቡ አቅጣጫዎች ዙሪያ ለተማሪዎች መወያያ የተዘጋጀ ሰነድ**

መስከረም 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ



# ክፍል አንድ

## 1. አጠቃላይ ሁኔታ

### 1.1. መግቢያ

- ትምህርት የመምህራንና የትምህርት ቤት ስራ ብቻ አይደለም።
- ሁሉም ባለድርሻ አካላት በጋራ የሚተባበሩበት የህብረት ስራ ነው።
- ከነዚህ ባለድርሻ አካላት ውስጥ ራሳቸው ተማሪዎች ትልቁን ድርሻ ይወስዳሉ ምክንያቱም የሚማሩት ራሳቸው ስለሆኑ።
- በመማር ማስተማር ሥራ ውስጥ የተማሪዎች የመማር፣ የማወቅና የመመራመር ተነሳሽነት ማደግ የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል።
- ሀገራችን በእውቀትና ክህሎት የዳበረ እንዲሁም በእኩልነት፣ በወንድማማችነትና እህትማማችነት መከባበርና መደማመጥ አስተሳሰብና ስነምግባር የታነፀ ትውልድ በእጅጉ ያስፈልጋታል።



# የቀጠለ

- ይህ ትውልድ ደግሞ ከየትም የሚመጣ ሳይሆን አሁን ያለው ትውልድ ነው ማለትም እናንተ ናችሁ።
- ይህንን በማመን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለትምህርት ጥራት መረጋገጥና ለሀገር ግንባታ መሰረት የሆኑትን የነገ ሀገር ተረካቢ ተማሪዎች ልዩ ትኩረት በመስጠት የተለያዩ ስራዎችን በመስራት ላይ ይገኛል።
- በዚህም አበረታች ውጤቶችን እያስመዘገብን እንገኛለን፤ ለማስታወስ ያህል በ2015 ትምህርት ዘመን በተመዘገበው የተማሪዎች ውጤት እና በተዘጋጀው ከተማ አቀፍ የሳይንስ ፈጠራና ኤግዚብሽን ፌስቲቫል ላይ በአይናችን ያየናቸው የተማሪዎች የፈጠራ ሥራዎች አበረታችና ወደፊት ለምናልመው የሀገራችን እድገት ተስፋ ያለን መሆኑን ያመለክታል።



# የቀጠለ

- በመሆኑም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የትምህርት ስራውን ከመምራት ባሻገር ለተማሪዎች የማበረታቻ ሽልማቶችን በመስጠት ውጤታማነት እያደገ እንዲሄድ ሲያደርግ ቆይቷል ይህ ተግባር በ2016 ትምህርት ዘመንም ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል።
- ይሁን እንጂ በ2015 ትምህርት ዘመን በተማሪዎች ውጤት እና ስነምግባር የሚያበረታቱ ሁኔታዎች ቢኖሩም በሚጠበቀው ልክ የተማሪዎች ውጤትና ስነምግባር አልተለወጠም።
- አሁንም ከዝቅተኛው የክፍል ማለፊያ ውጤት 50 ፐርሰንት በታች ውጤት ያላቸው ተማሪዎች ቁጥር ከፍተኛ ነው፤



# የቀጠለ

- በስነምግባርም ቢሆን ትምህርትን ባግባቡ ካለመከታተል ጀምሮ ትምህርት ቤትን እስከመረበሽ የደረሰ ብልሽት የነበረባቸው ተማሪዎች ቁጥርም ቀላል የሚባል አልነበረም።
- በ2016 የትምህርት ዘመን አዲሱ የቅድመ 1ኛ እና 2ኛ ደረጃ ስርአተ ትምህርት ከሙከራ ወደ ሙሉ ትግበራ የሚሸጋገርበት አመት ስለሆነ ከነበሩት አመታት በበለጠ የተማሪዎች ጥረትና ተነሳሽነት የሚፈለግበት ዓመት ነው።ስለዚህ ተማሪዎች ከችግሮቻቸው ተላቀው በውጤትና ስነምግባር ከፍተኛውን ደረጃ እንዲያስመዘግቡ ለማድረግ በቅድሚያ በጥንካሬዎቻችንና በድክመቶቻችን ዙሪያ ተወያይተንና ተማምነን የተማሪዎችን የዲስፒሊን መመሪያ በማክበር ትምህርታችንን ለመማር እንድንችል ይህ የውይይት መድረክ እንደሚከተለው ተዘጋጅቷል።



## 1.2. አላማና አስፈላጊነት

- የትምህርት ጥራት እንዲረጋገጥ ሁሉም ተማሪዎች ተቀራራቢ ውጤትና ስነምግባር ሊኖራቸው ይገባል።
- በመሆኑም ይህንን ውጤት ለማስመዝገብ በጥንካሬዎቻችንና ድክመቶቻችን ላይ ተወያይተን ማስተካከል ስለሚገባንና የማያስተካክል ተማሪም ካለ የተጠያቂነት ስርአት በማስፈን ለብዙሃን ተማሪዎች ሲባል ችግር ባለባቸው ላይ አስፈላጊውን የእርምት እርምጃ በመውሰድ የ2016 ትምህርት ዘመን መማር ማስተማሩን ውጤታማ ለማድረግ ነው።

# 1.3. የሚጠበቅ ውጤት

- በውይይቱ ተማሪዎች ስለመብትና ግዴታቸው የነበራቸው ግንዛቤ ያድጋል፣
- የተማሪዎች ስነምግባር ተሻሽሎ ሰላማዊ መማር ማስተማር ይፈጠራል፤
- የ2016 ትምህርት ዘመን በከፍተኛ ውጤት ይታጀባል፣
- የተማሪዎች ዙሪያ መለስ ተሳትፎ ያድጋል፣
- በተማሪዎችና ትምህርት ማህበረሰቡ መካከል ወንድማማችነትና እህትማማችነት እሴት ይጠናከራል፤

# ክፍል ሁለት

## 2. የተማሪዎች የ2015 ትምህርት ዘመን አፈፃፀም ነባራዊ ሁኔታ ግምገማ

### 2.1. መንግስት ለትምህርት እና ለተማሪዎች የሰጠው ትኩረት

#### 2.1.1. ተማሪዎች የትምህርት ቁሳቁሶቻቸው እንዲሟሉላቸው ስለመደረጉ

- ወላጆች በተለያዩ የትምህርት ቁሳቁሶች ወጪ እንዳያስቡና ተማሪዎችም ትኩረታቸው ትምህርታቸው ላይ ብቻ እንዲሆንና ውጤታማ እንዲሆኑ የከተማ አስተዳደሩ በቢሊየን ብር በሚተመን ከፍተኛ ወጪ የተማሪዎች ደብተር፣ ዩኒፎርም፣ ምገባ እና ሌሎች ቁሳቁሶችን እያሟላ ይገኛል፡፡



የያዝናቸውን የልማትና የመልካም አስተዳደር ግቦች ለማሳካት 140.29 ቢሊዮን ብር በጀት ሲፀድቅ።

## ሀ) ደብተር ስርጭትን በሚመለከት፡-

❖ከቅድመ አንደኛ እስከ 12ኛ ክፍል ላሉ በመንግስት ትምህርት ቤቶች ለሚማሩ ተማሪዎች በ2015 ዓ.ም የትምህርት ዘመን 6,483,560 የመማሪያ ደብተር በትምህርት ቢሮ በኩል ስርጭት ተከናውኗል።



## ለ) ዩኒፎርም ስርጭት በሚመለከት፡-

- ከቅድመ 1ኛ እስከ 2ኛ ደረጃ ላሉ ለ803,658 ተማሪዎች የደንብ ልብስ (ዩኒፎርም) በትምህርት ቢሮ በኩል ስርጭት ተከናውኗል።
- አንዳንድ ተማሪዎችም ስልጣኔ እየመሰላቸው ዩኒፎርሙን ከጥራት ደረጃው በታች እያበላሹ፣ እየቀደዱና እያጠበቡ መልበሳቸው፣





## 2.1.2. የ ቅድመ 1ኛ እና 1ኛ ደረጃ ተማሪዎች ምገባን በተመለከተ፡-

- በትምህርት ስራችን ላይ እያጋጠሙ የነበሩ የትምህርት ተሳትፎ፣ ፍትሃዊነትና ተጠቃሚነት፣ ብክነትና ጥራት ችግሮች እንዲሁም በተማሪዎች ዘንድ የሚስተዋለውን የሥርዓተ-ምግብ ተግዳሮቶች በተለይም ደግሞ በርካታ ተማሪዎች በተለያዩ ማህበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ምክንያቶች እና በወላጆች ዝቅተኛ የኑሮ ሁኔታ የተነሳ ወደ ትምህርት ገበታ ያለመምጣት፣ማርፈድ፤ መጠነ ማቋረጥና መድገም ሁኔታ በስፋት በማጋጠሙ የተማሪዎች ምገባ ፕሮግራምን ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ስለነበር መንግስት በከፍተኛ ቁርጠኝነት ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡
- በዚህም መርሃ ግብር ከቅድመ 1ኛ ደረጃ ጀምሮ 1ኛ እና መካከለኛ ደረጃ ድረስ በቀን ሁለት ግዜ  ቁርስና ምሳ እየተመገቡ በመሆኑ በትምህርት ስራችን ላይ መሰረታዊ የሚባል ለውጥ አምጥቷል፡፡



## የቀጠለ

❖በአጠቃላይ ለ701,000 ተማሪዎች አገልግሎቱን መስጠት ተችሏል።

❖ይህን የምገባ አገልግሎት የሚያቀርቡ በማህበር የተደራጁ 16,278 መጋቢ እናቶች ትልቅ የስራ እድል የተፈጠረላቸዉ ሲሆን ከተማሪዎቹ ባሻገር በወላጆቹ ዙሪያ ያሉ ቤተሰቦችም ተጠቃሚ ሆነዋል።

❖የምገባ ስርዓቱ የፈጠረው አዳዲስ ፍላጎቶች በመኖራቸው በዚህ ዓመትም መርሃ ግብሩ ውጤታማ ለማድረግ በርካታ ስራዎች ተከናውነዋል።

❖ለአብነት ያህል 687 የምገባ አገልግሎት ቁጥጥርና ክትትል ባለሙያዎች በየት/ቤቱ መመደባቸው፤

❖ለመጋቢ እናቶች የዋጋ ማስተካከያ መደረጉ፤

❖ የጤና ባለሙያዎች በየት/ቤቱ  በቋሚነት እንዲመደቡ መደረጉ፤

❖እንዲሁም የተለያዩ ለምገባው አገልግሎት የሚውሉ ጠረጴዛ፣  ወንበር፣  ምግብ ማብሰያ ድስቶች እና ሌሎች ግብአቶችን በመንግስት እና ከተለያዩ ግብረ-ሰናይ ድርጅቶች ጋር በጋራ በመተባበር የሟሟላት ስራ መሰራት ተችሏል።





## የቀጠለ

- እነዚህ ስራዎች በመሰራታቸው ምክንያት  የተማሪ ተሳትፎ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱ፤
- የሚያረፍዱ እና የሚቀሩ እንዲሁም የሚያቋርጡ ተማሪዎች በመሰረታዊነት መቀነስ መቻሉ፤
- የተማሪዎች አካላዊ እና አእምሮአዊ ዕድገት ላይ አዎንታዊ ለዉጥ ማምጣቱ፤
- የተማሪዎች የስነ-ልቦና ችግር መቅረፉ፤
- የተማሪዎች ውጤት በማሻሻል ረገድ አወንታዊ አስተዋፅኦ ማድረጉ፣
- የተማሪ ወላጆች ያላቸውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር በመቅረፍ እፎይታ የሰጠ ተግባር ሆኗል።
- ይሁን እንጂ ምገባ መርሃ ግብሩ ላይ አሁንም በርካታ ችግሮች አሉ፤ ለአብነት፤-
    - የመጠጥ ውህ አቅርቦት ችግር፣
    - የኤሌክትሪክ ሃይል አቅርቦት እጥረት ፣
    - የመመገቢያ እና ምግብ ማብሰያ አዳራሽ እጥረት፣
    - ተመጋቢ ተማሪዎች መሰረታዊ የንፅህና መመሪያዎችን እንዲከተሉ አለማድረግ፤
    - ተማሪዎች በምገባ ሂደት ሥርዓት ጠብቀው አለመስተናገድ ፣
    - የተመጋቢ ተማሪዎች አቴንዳስ በአግባቡ አለመያዝ፣
    - ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተመጋቢዎች ቅድሚያ አለመስጠት፣

## የቀጠለ

- ❖የውሃ ማጠራቀሚያ ታንከር በንፅህና አለመያዝ፤
- ❖የተማሪዎች መመገቢያ ክፍል ለሕጻናት ቁመት ተስማሚ፣ በቂ፣ ምቹ መቀመጫና ጠረጴዛ አለመኖር፤
- ❖በተማሪዎች መመገቢያ ክፍል ንጹሕ የመጠጥ ውኃ አቅርቦት፣ በቂ መጠጫና የውኃ ማስቀመጫ ሥፍራ አለመኖሩ፣
- ❖በአንዳንድ ትምህርት ቤቶች በከተማ ደረጃ የተዘጋጀው የምግብ ዝርዝር (ሜኑ) በአግባቡ አለመተግበር፣
- ❖በየትምህርት ቤቱ የተመደቡትን የምገባ አገልግሎት ቁጥጥር እና ክትትል ባለሞያዎች ምቹ የስራ ሁኔታ አለመፍጠር እና ድጋፍ አለማድረግ፤
- ❖በመሆኑም እነዚህ እና መሰል ችግሮች ለመፍታት ተማሪዎችና ሁሉም ባለድርሻ አካላት አስፈላጊውን ትብብርና ርብርብ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።



- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በተማሪዎች ምገባ ፕሮግራም በአለም አቀፍ ደረጃ መሸለሟን በማስመልከት የኢፌድሪ ፕሬዘዳንት ክብርት ሳህለ ወርቅ ዘውዴ እና የአዲስ አበባ ከንቲባ ክብርት ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ለውጤቱ ለክቡር ዶ/ር ዘላለም ሙላቱ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ሃላፊ እውቅና ሲሰጡ፡፡

**የምገባ ፕሮግራም አለማቀፍ ዕውቅና የተገኘበት**



# 2.1.3. ትምህርት ለትውልድ › የተሰኘ ንቅናቄ

- ትምህርት ቤቶች ለተማሪዎች ምቹ፣ ሳቢና ደረጃቸውን እንዲጠብቁ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ትምህርት ለትውልድ በሚል መርህ በህብረተሰቡ ተሳትፎ ትምህርት ቤቶች እየታደሱና ግብአታቸው እየተሟላ ይገኛል ።
- ተማሪዎችም ለዚህ ስራ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ማድረግ ይገባቸዋል።



"ትምህርት ለትውልድ!" በሚል መሪ ቃል የትምህርት ቤቶች መሰረተ ልማት ንቅናቄ ማስጀመሪያ መርሃ ግብር ላይ ክብርት ክንቲባ አዳነች አቤቤ በሻሌ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ G+4 የመማሪያ ክፍል ህንጻ ፣ የስፖርት ሜዳ ፣ የቤተ መጻህፍት ፣ ላብራቶሪና አይሲቲ መዕከል ግንባታ የመሰረት ድንጋይ ሲያስቀምጡ ።

# 2.1.3. ትምህርት ለትውልድ › የተሰኘ ንቅናቄ

## 2.2. የመማር ማስተማር ሁኔታ ግምገማ

❖ በማማር ማስተማር ውስጥ ስርዓተ ትምህርት፣ መምህራን እና ተማሪዎች የማይነጣጠሉ የትምህርት ጥራት ዋና ምሰሶዎች ናቸው፡፡

❖ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ አዲሱ ስርአተ ትምህርት መሠረት የመማሪያ እና ማስተማሪያ መፅሐፍት አዘጋጅቶ ስራ ላይ በማዋል ረገድ ግንባር ቀደም መሆኑ ይታወቀል፡፡

❖ አዲሱ ስርዓተ ትምህርት ጥራትን፣ ሙያ እና የቀለም ትምህርትን በማጣመር እንዲሁም የተማሪዎች ውጤትና ስነምግባር መሻሻልን ግቡ አድርጎ የተቀረጸ ነው፡፡

❖ይህንን ስርአተ ትምህርት ወደ ተማሪዎች ለማድረስ መምህራን የማይተካ ሚና ስላላቸው በአዲስ መልክ ስለተዘጋጀው ስርዓተ ትምህርትየመጽሃፍት ትዉዉቅ በማድረግ በሁሉም የትምህርት ዓይነት በቂ መምህራን ተሟልተው ከሙከራ ትግበራ እስከ ሙሉ ትግበራ እየተሰራ ነው፡፡



የ6ኛ ክፍል ተማሪዎች በአዲሱ ስርአተ ትምህርት ተምረው የሚኒስትረ ፈተና ሲወስዱ ዶ/ር ዘላለም ሙላቱ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ሃላፊ እና ም/ቢሮ ሃላፊ ጉብኝት ሲያደርጉ



የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የአዲሱን ስርዓተ ትምህርት አተገባበር በተመለከት ከርዕሰነ መምህራን ጋር ውይይት ሲያካሂዱ፡፡

# የቀጠለ



- በ21ኛዉ ክፍለ ዘመን በሀገር አቀፍ እና አለም አቀፍ ደረጃ በቀለም ትምህርት፣ በክህሎት እና ቴክኖሎጂ ተወዳደሪ መሆን ከተማሪዎች የሚጠበቁ ውጤቶች ናቸው፡፡
- እንደ ዩኔስኮ (UNESCO ) አገላለፅ መማርን በአራት አንኳር ጉዳዮች ይገልፃል ፤-
  - “learn to know (ዕዉቀት ለማግኘት) ፤
  - learn to do, (በተግባር ላይ ማዋል)
  - learn to live together (አብሮነትን ወይም ጥሩ ማህበራዊ ትስስር ለመፍጠር) እና
  - learn to be.” (ራዕይ እና አለማችንን ለማሰካት) መሆኑን ያሳየናል፡፡

# የቀጠለ

- ከላይ የተቀመጡትን ሀሳቦች በትምህርት ቤቶቻችን ነባራዊ ሁኔታ ስንቃኘው ተማሪዎች የትምህርት ቤታቸውንም ሆነ የራሳቸውን ራዕይ፤ ለተልዕኮ እና እሴቶች ለይቶ በመገንዘብ በውጤት እና ስነምግባር ማሻሻል ላይ በ4ዮሽ ስምምነት ፊርማ መሰረት ግብ አስቀምጠው በማቀድና እቅዳቸውን ከግብ ለማድረስ በመስራት በኩል የሚያበረታታ ሁኔታ ቢታይም በአንፃሩ በርካታ የሚስተዋሉ ችግሮችም አሉ።
- በ21ኛው ክፍለ ዘመን ራዕይ፣ እሴትና ተልእኮ የሌለው ተማሪ መጨረሻው ከአለም ውድድር ውጪ ሆኖ የሰቆቃ ህይወትን የሚገፋ እንደሚሆን ሳይታለም የተፈታ ነው።

# የቀጠለ

❖በድጋፍ እና ክትትል በተገኘ መረጃ መሠረት የክፍል ስራ፤ የቤት ስራ፣ የቡድን ስራ፣ ቤተ-መፃህፍት ገብቶ ማንበብ፣ በቤተ-ሙከራ ገብቶ ተግባራዊ ትምህርት መውሰድ፣ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን ከመምህራን ጋር መስራት እና የመሳሰሉ ተግባራት ላይ የሚታየው የተማሪዎች ጥረት በቂ የሚባል አይደለም፡፡

❖ በየትምህርት ቤቱ ቁጥራቸው ጥቂት የማይባሉ ተማሪዎች ትኩረታቸውን ትምህርት ላይ ከመድረግ ይልቅ ጊዜያቸውን በአልባሌ ጉደይ ላይ ያውላሉ፣ ያረፍዳሉ፣ ይቀራሉ፣ በአካባቢው በሚገኝ የጫወታ ቤቶች ይውላሉ በዚህም ምክንያት የትምህርት ውጤታቸው ዝቅተኛ ነው ፡፡

❖ 50 ፐርሰንት ውጤት አምጥቶ ከክፍል ወደ ክፍል ማለፍ አለማቀፍ ተወዳዳሪ ተማሪ እንደማያደርግ መታወቅ አለበት፡፡





## 2.3. የተማሪዎች ተሳትፎ ሁኔታ ግምገማ፡-

ተማሪዎች በበርካታ የትምህርትና የልማት ስራዎች መሳተፍ አለባቸው ። ከዚህ ተሳትፎአቸው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በርካታ ቁምነገሮችን እየተገነዘቡና እየለመዱ ያድጋሉ። በዚህም በ2015 ትምህርት ዘመን በትምህርት ቤቶች ክበባትና በልዩ ልዩ ክበባቶች ውስጥ የነበራቸው ተሳትፎ የሚበረታታ ቢሆንም በሁሉም ተማሪዎች ተሳትፎ የተከናወነ አልነበረም። በብዙ ቦታዎች ተሳትፎ ላይ የሚታዩት ጥቂት ተማሪዎች ብቻ ናቸው።

ሁሉም ተማሪዎች ተሳትፈውበታል የሚባለው በብሄር ብሄረሰብና አረንጓዴ ልማት እንዲሁም በበጎ አድራጎት ስራ ለተቸገሩ ወገኖች ያላቸውን በማበርከት በኩል አበረታች ተሳትፎ ነበራቸው።

## 2.4. የተግባቦት ሁኔታ ግምገማ

- ተግባቦት /communication/ ማለት በሰዎች መካከል የሚደረግ የመልእክት ልውውጥ እና መረጃ የመሰብሰብ፣ የመተንተን እና የማሰራጨት ዘዴ ነው።
- ተግባቦትን ለማዳበር ከሚረዱ ጠባያት ዋነኛው ጥሩ አድማጭነት ነው።
- ሰዎች በሚናገሩበት ሰዓት ተናግረው እስኪጨርሱ በጥሞና የማዳመጥና የመረዳት እድል መስጠት አስፈላጊ ነው።
- በ2015 ትምህርት ዘመን ይህ የተግባቦት ሁኔታ በትምህርት ቤት ደረጃ ሲገመገም አብዛኞቹ ትምህርት ቤቶችና ተማሪዎች በመልካም መግባባት የመማር ማስተማር ስራቸውን ሲያከናውኑ እንደነበር በርካታ የክትትል ሪፖርቶች ያመላክታሉ።
- በአንፃሩ በአንዳንድ ትምህርት ቤቶች የሚታዩ ጥቂት ተማሪዎች ሌሎች ተማሪዎችን ወይም መምህራንን በጥሞና የማዳመጥ ችግር ይስተዋልባቸዋል፣
- አጣርተው ሳይሰሙ ለማውራት ይቸኩላሉ፣ በእረፍትና ምሳ ሰአትም ስለ ትምህርታቸው መነጋገር ቀርቶ ስለማያገባቸውና ለሃገርም ሆነ ለራሳቸው ምንም ጥቅም በሌላቸው ጉዳዮች ላይ ያተኩራሉ፤
- እነዚህ ጉዳዮች ተባብሰውም ወደ ፀብና አለመግባባት ሲያደርሳቸው ይታያል። በመሆኑም እነዚህ ተማሪዎች በቀጣዩ ትምህርት ዘመን መርህን መሰረት ያደረገ የተግባቦት ክህሎትን ማዳበር ይጠበቅባቸዋል። ይህ ካልሆነ ግን ወደ አላስፈላጊ የቅጣት እርምጃ ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ።

## 2.4. የተግባቦት ሁኔታ ግምገማ

**ተማሪዎች ከማህበረሰቡ ጋር ያላቸው መግባባት ለሚከተሉት ጥንካሬዎች ያበቃቸዋል፡፡**

- የተሻለ ፈጠራና ተመራማሪ ዜጋ ማፍራት ማስቻሉ፣
- የትምህርት ቤት ማህበረሰቡን  እንደ ቤተሰብ በመቁጠር የመጠበቅና የመንከባከብ  ግዴታ እንዳለበት መረዳት መኖሩ፣
- በማህበረሰቡ ጥሩ  ሆኖ  ለመገኘት ጥረት ማድረግ ተገቢ መሆኑን  እንዲረዳ ማስቻሉ እና ሌሎች ጥንካሬዎች አሉት፡፡

**በአንፃሩ ከማህበረሰቡ ጋር የመግባባት ድክመት ያለባቸው ተማሪዎች የሚፈጠርባቸው ችግሮች**

- ራስ ወዳድ ዜጋ እንዲፈጠር ያደርጋል፣
- ከባህሉና ከማህበረሰቡ  የተለየ ሩቅ ናፋቂ  ያደርጋቸዋል፣
- ከመግባባት ይልቅ  ግጭት ፈጣሪ  እንዲሆን ያደርጋል ፣
- ሱሰኛነትን ይፈጥራል፣ ስለዚህ እነዚህን ችግሮች ቀድሞ ማስተካከል ያስፈልጋል፡፡

## 2.4.5 የእርስ በርስ የተማሪዎች ተግባቦት ሁኔታ

ተማሪዎች የተግባቦት ክህሎት ሊኖራቸው የሚገባው ለሚከተሉት ዋና ዋና ጉዳዮች ነው

- ሀ ለቀለም ትምህርታቸው ውጤታማነት
- ለ ለሙያ ምርጫቸው ዝግጁነት
- ሐ ለማኅበራዊና ሥነ ልቦናዊ ዕድገት
- መ በጥልቀት ለማሰብ፣
- ሠ ለብዝሀ ባህል መዳበርና ለመሳሰሉት ያግዛቸዋል

## በተማሪዎች መካከል የሚስተዋሉ የተግባቦት ክፍተቶች የሚያስከትሉት ችግር

- በተማሪዎች መካከል  አላስፈላጊ ጭቅጭቅና ንትርኮች መፍጠር፣
- የክፍል ውስጥ ስነስርዓትን ያለማክበር በክፍል ውስጥ መረበሽና መጮህ፣
- ሴት ተማሪዎችን መተንኮስና ማስፈራራት፣
- ከሌሎች ተማሪዎች ጋር በመግባባት አለመስራትና አለመማር ችግሮች በብዛት ይፈጠራሉ።

## 2.5. የተማሪዎች ስነምግባር ሁኔታ ግምገማ

### 2.5.1. በጥንካሬ የሚታዩ

- ❖ ተማሪዎች በጥሩ ስነምግባር ታንፀው ብቁና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ዜጎች በመሆን የራሳቸዉን የወደፊት መጻኢ እድል ማሳካት ይጠበቅባቸዋል፣
    - ❖ ከዚህ አንፃር በ2015 ትምህርት ዘመን አብዛኛዎቹ ተማሪዎቻችን በብቁ ስነምግባር አመቱን አጠናቀዋል።

❖ ከዚህ አኳያ በርካታ ተማሪዎች የትምህርት ቤት ቅጥር ግቢአቸውን ሥነ-ሥርአት እና የተማሪዎች የስነምግባር ደንብን በማክበርና በማስከበር፣ ያላቸውን የጥናት ልምድና የውጤታማነት ሚስጥር ለሌሎች በማካፈል የመሪነት ሚና የሚጫወቱ ተማሪዎች   ነበሩ።

- ❖ እንዲሁም የወደፊት ህልማቸውን ብሩህ ለማድረግ ጊዜያቸውን በአግባቡ የሚጠቀሙ፣ ጠንክረው የሚያጠኑ፣ ወላጆቻቸውን እና የት/ቤት ማሕበረሰቡን የሚያከብሩ፣ መጥፎ የአቻ ግፊትን የሚቋቋሙ፣ ለጊዜያዊ ችግሮች የማይሸነፉ፣ የት/ቤቶቻቸውን ህግና ደንብ የሚያከብሩ፣ የማያረፍዱ፣ ከአቅም በላይ ባልሆነ ምክንያት ከት/ቤት የማይቀሩ፣ የተሰጣቸውን የክፍልና የቤት ስራ ጠንቅቀው የሚሰሩ፣ በተለያዩ የፖለቲካ አስተሳሰቦች የማይወሰዱ፣ ለፀረ-ሰላም ሃይሎች አላማን በመቃወም ትርጉም ያለው ጥንካሬ የነበራቸው ተማሪዎች ነበሩ፡

## 2.5.2. በተማሪዎች ስነምግባር ላይ የታዩ ድክመቶች

- ❖ ቁጥራቸው ቀላል የማይባል ተማሪዎች ለትምህርት ብለው ከቤት በመውጣት በአልባሌ ቦታ መዋል፣
    - ❖ የት/ቤቶቻቸውን ህግና ደንብ ያለማክበር፣
- ❖ ስለህይወታቸው ግልጽ ራዕይ አለመያዝ፣
    - ❖ ከመምህራኖቻቸውና ከት/ቤቱ ማሕበረሰብ ጋር አለመስማማት፣
- ❖ በአጥር መዝለል ፣ አርፍዶ መግባት፣ ተደብቀው ከክፍል መጥፋትና ክፍል ውስጥ ተገኝቶ ትምህርት ያለመለከታተል፣
    - ❖ የተሰጣቸውን የከፍልና የቤት ስራ አለመስራት፣
- ❖ ሰለሚያመጡት የት/ት ዉጤት አለማሰብና የሌሎችን ተማሪዎች የመማር ሁኔታ ማወክ ፣
    - ❖ ወላጆቻቸውን እና መምህራኖቻቸዉን አለማክበር፣
- ❖ በተለይም በ2015ዓ.ም በከተማ ደረጃ በአንዳንድ ትምህርት ቤቶች በተፈጠረው የፀጥታ ችግር ምክንያት የተማሪዎች የስነ ምግባር ግድፈቶች ጎለተው ታይተዋል፤

# የቀጠለ

❖በዚህም የትምህርት ቤቶች ህንጻ በርና መስኮት እንዲሁም መገልገያ ቁሳቁሶችን በማውደም በተቋማት ላይ የሀብት ውድመት አስከትለዋል፤

❖ ሰላማዊ መማር የማስተማር ሂደቱም እንዲታወክ አድርገዋል፤

❖የፈተና ሥርቆት ወይም ኩረጃ፤ ረብሻ፤ የትምህርት ግብዓት ስርቆት፣

❖በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ እና ከትምህርት ቤት ወጭ አደገኛ ዕፆች መጠቀም ሲጋራ ማጨስ፣ ጫት መቃም፣ አልኮል መጠጥ መጠጣት፣ ሐሺሽና የመሳሰሉትን መጠቀም፤

❖የእርስ በርስ የቡድን ፀቦች፤ እና የመሳሰሉ በርካታ የሥነምግባር ጥሰቶች ተፈጽመዋል፡፡

❖እንዲሁም ጥቂት በሆኑ ትምህርት ቤቶችም ትምህርትን ከፖለቲካና ሃይማኖት ጋር በማያያዝ ፀረ-ሠላም የሆኑ አካላትን የፖለቲካ ዓላማ ለማስፈጸም ተልእኮ ይዘው በመጡ አካላት አማካኝነት የመማር ማስተማሩ ሂደት እንዲደናቀፍ በርካታ ተግባራቶች ተፈፅመዋል፡፡

❖መንግስት በሌለው አቅም የገነባቸው ትምህርት ቤቶች ሃብት እና ንብረት ተሰባብረዋል ወድመዋል፡፡

❖በተማሪዎች፤ መምህራንና ር/መምህራን ላይ ጉዳት ደርሷል፤

❖እነዚህ የስነምግባር ግድፈቶች በቀጣይ ሊስተካከሉ ይገባል፡፡





# ለዚህ የስነ ምግባር ችግር ምክንያቶቹ

- በትምህርት ቤት አካባቢ ያሉ አዋኪ ሁኔታዎች፣ ቁማር ቤቶች፣ ሺሻና ጫት ቤቶች፣ በትምህርት ቤቶች አጥር ላይ የነበሩ ህገወጥ ተለጣፊ ሱቆችና የመሳሰሉት ነበሩ፣
- በደላላዎች አስኮብላይነት በሴት ተማሪዎች ላይ የሚፈጸሙ ወሲባዊ ጥቃቶች፣
- ጐጂ ለሆኑ መጤ ባህሎች መጋለጥና ለአገራችን ዕድገትና ለህዝባችን መሻሻል አስተዋጾ የሌላቸውን በዓላትን በትምህርት ቤት አካባቢ ማክበር ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

**የገጠሙን ፈተናዎችና የፈታንበት አግባብ**

## ሀ) የተወሰኑ ስነምግባር የጎደላቸው ተማሪዎች የፈጠሩት ረብሻ

- ❖ ብዝሃነትን አለማክበር፣ የትምህርት ሴኩላሪዝም መርህን በመጣስ የግል እምነትን፣ የፖለቲካ አስተሳሰብን እና የብሄር ጽንፈኝነትን በመያዝ ወደ ትምህርት ቤቶች በመግባት ሰንደቅ አላማን ምክንያት በማድረግ የእርስ በርስ የቡድን ፀቦች ተስተውለዋል፡፡

# የቀጠለ

- በተወሰኑ ትምህርት ቤቶችም ትምህርትን ከፖለቲካና ሃይማኖት ጋር በማያያዝ ፀረ-ሠላም የሆኑ አካላትን የፖለቲካ ዓላማ ለማስፈጸም ተልእኮ ይዘው በመጡ አካላት አማካኝነት የመማር ማስተማሩ ሂደት እንዲደናቀፍ በርካታ ተግባራቶች ተፈፅመዋል፡፡

- መንግስት እና ህዝብ  የገነባቸው ትምህርት ቤቶች ሃብት  ንብረት ተሰባብረዋል ወድመዋል፡፡

- በተማሪዎች፤ መምህራንና ር/መምህራን ላይ ጉዳት ደርሷል፤  ይህ እኩይ ተግባር ሲፈፀም ችግሩን ለማስቆም የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ሲያደርጉ የነበሩ በርካታ ተማሪዎች፣ እንደነበሩ ሁሉ ጥፋቱን ከማስቆም ይልቅ እንዲባባስ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ሲደግፉ የነበሩ ተማሪዎችም ነበሩ፡፡

- ይሁንና ይህን ፈተና ከብዙሃኑ ሰላም ወዳድ ተማሪዎችና  መምህራን እንዲሁም ወላጆች ጋር በመወያየት እኩይና ፀረ-ህዝብ ሃይሎች ያሰቡት ሳይሳካ ሊከሽፍ ችሏል፡፡

## ለ) የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ውጤት መውረድ ሌላው የገጠመን ፈተና ነው

- የ12ኛ ክፍል ፈተና በዩኒቨርሲቲዎች እንዲሰጥ በመደረጉ በ2014 ትምህርት ዘመን የነበረው ውጤት በከፍተኛ ደረጃ የወረደ ነበር።
- ምክንያቱም ቀላል የማይባል ቁጥር ያላቸው ተማሪዎች ለራእያቸው አይሰሩም፣ ለውጤታቸውም አያስቡም፤ በመሆኑም ኩረጃን እንደ ሌብነት አይቆጥሩትም ነበር፤ ይልቁንም ኩረጃ ስልጣኔ እየመሰላቸው ጎበዝ ተማሪዎችን ጭምር እያሳነፉ የሚውሉ ተማሪዎች ቁጥር ከፍተኛ መሆኑ ሌላው ፈተና ነበር።
- ሆኖም በ2015 ትምህርት ዘመን ለነበሩ የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ከፍተኛ ጥንቃቄ በማድረግ እንዲፈተኑ ተደርጎ ውጤት በመጠባበቅ ላይ እንገኛለን ።
- ነገርግን ውጤት በአንድ አመት የሚለወጥ ስራ አይደለም ሁሉም ተማሪ ከስር ጀምሮ ኩረጃን ተፀይፎ፣ ራእይ ቀርፆ፣ በጊዜ የለንም መንፈስ በትጋት መስራት ካልቻለ የሚለወጥ አይደለም ስለሆነም ተማሪዎች በትምህርታችሁ ትጋትን መጨመርና በራስ ጥረት ብቻ ችግሮችን ለማለፍ መጣር አለባችሁ።

## ክፍል ሶስት

# 3. በ2016 ትምህርት ዘመን ተማሪዎች ሊከተሉት የሚገባ መርህ

### 3.1.የመንግስትን ድጋፍ ባግባቡ የመጠቀምና ውጤታማ የመሆን መርህ መከተል፣

- ከላይ እንደተገለፀው መንግስት ለተማሪዎችና ለትምህርት በርካታ ድጋፎችን እያደረገ ነው ስለዚህ እነዚህ ድጋፎች ውጤት ማምጣት ካለባቸው ተማሪዎች እነዚህን ድጋፎች ባግባቡ ጥቅም ላይ ሲያውሉት በመሆኑ ዩኒፎርማቸውን፣ ደብተራቸውን እና ሌሎች ግብአቶችን ባግባቡና በቁጠባ በመጠቀም ውጤታማ የመሆን መርህን መከተል ይገባቸዋል ለዚህ መርህ መከበር የትምህርት ቢሮና በየደረጃው ያለ የትምህርት አመራር ሃላፊነቱን ወስዶ ችግር ያለበትን ስራ ማስተካከልና ተጠያቂነትን የማስፈን ስራ ይሰራሉ፡፡

## 2. የክፍል ውስጥ መማር ማስተማሩን ባግባቡ በመተግበር ውጤታማ የመሆን መርህ መከተል፣

- መማር ማስተማሩ ዋናው ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት የሚመጡበት አላማ ነው በመሆኑም ይህ አላማ እንዲሳካ በትምህርት ቤት ውስጥ የሚካሄዱ የመማር ማስተማር ተግባራት ጊዜያቸውን ጠብቀው ባግባቡ እንዲካሄዱ ተማሪዎች የበኩላቸውን ሚና መወጣት አለባቸው ራእይ ቀርፀው፣ መልካም እሴቶቻቸውን አዳብረው፣ ተልእኮአቸውን ተረድተው መማርን መርሃቸው በማድረግ በውጤትና ስነምግባር የተለወጡ ሊሆኑ ይገባል።

## 3.3. በተለያዩ ጉዳዮች ተሳትፎን የማሳደግ መርህ መከተል፣

- በትምህርት ቤቶች ውስጥ ተማሪዎች የሚሳተፉባቸው በርካታ ጉዳዮች አሉ፤ በትምህርት ቤት አመራር፣ በክበባት፣ በኮሚቴዎችና በጽዳትና ሌሎች የከተማ ግብርና፣ የበጎ አድራጎት እና የአረንገዴ ልማት ስራዎች ላይ መሳተፍ ክህሎታቸውን ያሻሽለዋል፣ የስራውን አለም ያውቁበታል ብቁና ተወዳዳሪ ዜጎች እንዲሆኑ መሰረት ስለሚሆናቸው ተሳትፎን ዋናው የተማሪዎች መርህ አድርጎ መውሰድ ያስፈልጋል።

## 3.4.ከትምህርት ማህበረሰቡ ጋር የሚኖር ውጤታማና ተገቢ ተግባቦት መርህ መከተል፤

- መማር ውጤታማ ነው የሚባለው ከሌሎች ባልደረቦች ጋር መልካም ተግባቦት መፍጠር ሲችል ነው፤ ተማሪዎች እርስ በርሳቸው፣ ከመምህራኖቻቸውጋር፣ ከወላጆች ጋር፣ ከትምህርት ቤቱ አመራሮችና ከአካባቢው ህብረተሰብ ጋር ትርጉም ያለው ተግባቦት መፍጠር ያስፈልጋቸዋል። ይህ ተግባቦትም ዲሞክራሲያዊና በወንድማማችነትና እህትማማችነት መርህ ላይ ያተኮረ መሆን ይጠበቅበታል።

## 3.5. ከስነምግባር ችግሮች በመለቀቅ ሞዴል ተማሪ ሆኖ የመገኘት መርህ መከተል፣

- አዲስ የተዘጋጀው የተማሪዎች የዲሲፕሊን መመሪያ በያዝነው 2016 ትምህርት ዘመን ባግባቡ ተግባራዊ ይደረጋል። ይህ መመሪያ ሲተገበር፡-
- ተማሪዎች መልካም ምግባርን በመላበስ ለህገራቸውና ለወገናቸው ተቆርቋሪ ችግር ፈችና መልካም ስነ ምግባር ያላቸው ዜጐች ሆነው እንዲቀረጹ ያስችላል፣
- ተማሪዎች የትምህርት ቤታቸውን ህግና ደንብ በማክበር በትምህርታቸው ውጤታማ እንዲሆኑ ያደርጋል፤
- ተማሪዎች ችግሮቻቸውን ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ በሃሳብ ክርክርና ውይይት ብቻ እንዲፈቱ ያስችላል።

# የቀጠለ

- ተማሪዎች መብታቸውንና ግዴታቸውን ጠንቅቀው በማወቅ በመማር ማስተማር ሂደቱ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ያበረታታል።
- ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ በሚቆዩበት ጊዜ በራስ የመተማመን መንፈስ በጋራ የመኖርና የመረዳዳት እና የመከባበር ባህል እንዲያዳብሩ ያደርጋል፣
- አሁን ላይ በጥቂት ትምህርት ቤቶች እየታየ ያለው በትምህርት ቤት ሃብትና ንብረት ላይ የሚደርሰው ውድመት በሥነምግባር ደንቡ መሰረት ህጋዊ እርምጃ በመውሰድ ይስተካከላል።
- ተማሪዎች ቴክኖሎጂን አላስፈላጊ በሆነ ሁኔታ እንዳይጠቀሙ እና በአግባቡ ጠቀሜታ ላይ እንዲያውሉ ያደርጋል።

መመሪያው በቀጣይ በስፋት የሚተዋወቅ ሆኖ በዚህ መድረክ ዋና ዋናዎቹን ለማንሳት ያህል የሚከተሉት ቀርበዋል፡፡

## ❖ተማሪዎች ሊኖራቸው የሚገባ መብት

- ❑ ተማሪዎች የመማር፣ ጠይቆ የመረዳትና የማወቅ መብት አላቸው፣
- ❑ ተማሪዎች ከማንኛውም ዓይነት የአካልና ሥነልቦና ጥቃቶች የመጠበቅ መብት አላቸው፣
- ❑ ተማሪዎች በት/ቤቱ የትምህርት ግብዓቶች የመጠቀም ወይም አገልግሎት የማግኘት መብት አላቸው፣
- ❑ ተማሪዎች የትምህርታቸውን ውጤትና የምስክር ወረቀት በወቅቱ የማግኘት መብት አላቸው፣
- ❑ ተማሪዎች ስርአትና ደህንነቱ በተጠበቀ ክፍል እና ት/ቤት የመማር መብት አላቸው፣
- ❑ ተማሪዎች ሃሳባቸውን የመግለጽና የመደመጥ መብት አላቸው፣

- ❑ ተማሪዎች ያለመሰደብ፣ የግል ምስጢራዊ ጉዳዮች የመጠበቅ መብት አላቸው፣
- ❑ ተማሪዎች ያታን መሰረት ካደረገ ጥቃት የመጠበቅ መብት አላቸው፣
- ❑ ተማሪዎች የት/ቤቱን ደንብና መመሪያ የማወቅና የማግኘት መብት አላቸው፣
- ❑ ተማሪዎች ከመምህራን ጋር ተገቢ የሆነ የመማር ማስተማር ግንኙነት በመፍጠር ድጋፍና እርዳታ የማግኘት መብት አላቸው፣
- ❑ ተማሪዎች የሚደርስባቸውን በደልና ቅሬታ በየደረጃው ላሉ የት/ቤቱ አካላት የማቅረብ መብት አላቸው፣
- ❑ ተማሪዎች ስለመምህራን የማስተማር ክህሎት በሚዛናዊነት የመገምገም አስተያየት ሲጠየቁ የመስጠት መብት አላቸው፣

# የቀጠለ

- ተማሪዎች ከመማሪያ ክፍል ውጭ የሚከናወኑ የተጓዳኝ ትምህርት ፕሮግራሞች ላይ የመሳተፍ መብት አላቸው፣
- በትምህርት ቤት ውስጥ ለተማሪዎች ከሚሰጠው የልዩ ልዩ የኃላፊነት ቦታዎች ላይ መምረጥና የመመረጥ መብት አላቸው፣
- ተማሪዎች ከት/ቤት ወይም በቅርብ ከሚገኝ የጤና ማዕከል የመጀመሪያ ዕርዳታ የማገኘት መብት አላቸው፣
- ተማሪዎች ልዩ የመማር ፍላጎታቸውን መሰረት ያደረገ አገልግሎት የማግኘት እና ከጥቃት የመጠበቅ መብት መብት አላቸው፣
- ተማሪዎች በት/ቤት የዕቅድ ዝግጅትና የአፈጻጸም ሪፖርት ላይ በተወካዮቻቸው አማካኝነት የመሳተፍ መብት አላቸው፣

# ግዴታዎች

- ት/ቤቱ በሚያወጣው የትምህርት ፕሮግራም መሠረት በሰአቱ መገኘት፣
- ያለበቂ ምክንያት አለማርፈድ እና አለመቅረት፣
- በሰንደቅ ዓላማ ሥነ-ስርአት ላይ መገኘትና መዘመር
- በተማሪዎች መካከል አላስፈላጊ ጭቅጭቅና ንትርኮች አለመፍጠር፤
- የክፍል ውስጥ ስነስርዓትን ማክበር በክፍል ውስጥ አለመረበሽ፣ አለመጮህ፣ መብራት አለማብራትና አለማጥፋት .... ወዘተ፣
- የግልና የጋራ ንፅህናን መጠበቅ፣
- መምህራንን እና የትምህርት ማህበረሰቡን ማክበር፣ በት/ቤቱ ውስጥ በተማሪዎች ላይ ጉዳት ያደርሳሉ ተብሎ ከተከለከሉ ሥፍራዎች እራስን ማራቅ፣
- በክፍል ውስጥ የሚሰጠውን ትምህርት በግልም ሆነ በቡድን በጥሞና መከታተል፣
- የክፍል ሥራ፣ የቤት ሥራ፣ የቡድን ሥራ የሚሰጡ የችሎታ መመዘኛዎችን ሠርቶ አጠናቆ በጊዜው ማቅረብ፣
- የት/ቤቱ ኃላፊዎችና መምህራን በአግባቡ የሚሰጡትን ድጋፍ ምክርና መመሪያ መፈፀም፣
- ከሌሎች ተማሪዎች ጋር በመግባባት መስራት፣
- በፈተና ወቀት ከተፈቀደላቸው ተማሪዎች በስተቀር ማንኛውንም የተከለከሉ ቴክኖሎጂዎችን ይዞ ወደ ክፍል አለመግባት፤
- የትምህርት ጊዜን በማይሻማ ሁኔታ ዕውቀቱንና ጉልበቱን ለትምህርት ቤቱና ለአካባቢው ህብረተሰብ አገልግሎት አለማዋል፣

# የቀጠለ

- ማንኛውንም የት/ቤቱ ንብረት የሆኑትን የመማሪያ መጽሐፍትን፣ መቀመጫ ወንበሮችን፣ ጥቁር እና ነጭ ሰሌዳ፤ የፕላዝማ ቴሌቪዥን ፤ሬዲዮ ፤ ኮምፒዩተሮች ፤ የኢንተርኔት መሰረተ ልማትና ቁሳቁሶችን፤ የመማሪያ ክፍሎችን፣ መስኮቶችን፣ እና ሌሎች የትምህርት ቤት ንብረቶችን በጥንቃቄ መያዝ ፣ መጠቀም እና እንዲበላሹ እና እንዲወድሙ አለማድረግ፣
- ሕጋዊ ባልሆኑ ስብሰባዎች ላይ አለመሳተፍ፣
- በተለያዩ የተጓዳኝ ክበባት መሳተፍ፣
- በትምህርት ሰዓት ያለ በቂ ምክንያት በት/ቤት ቅጥር ግቢ አለመዟዟር፣
- የት/ቤቱን አጥር ዘሎ አለመውጣት/አለመግባት/እቃዎችን በአጥር አለመቀበልና አለማቀበል፣
- ለትምህርት ቤቱም ሆነ ለትምህርት ማህበረሰቡ ታማኝ መሆን፣
- የት/ቤቱን ማህበረሰብና እራሱን ተላላፊ እና ተላላፊ ካልሆኑ በሽታዎች መጠበቅ፣ መከላከል፣
- በት/ቤት ቅጥር ግቢ መታወቂያ ይዞ መገኘት እና ሲጠየቅ ማሳየት፣
- የመንግስት ትምህርት ቤቶች የተማሪዎች ዩኒፎርም /የደንብ ልብስ/ የከተማ አስተዳደሩ ትምህርት ቢሮ በሚወስነው የጨርቅ ዓይነት፤ ጥራት እና ቀለም እና ስፌት ዲዛይን መጠቀም፣

# የቀጠለ

- መንግስታዊ ያልሆኑ እና የግል ትምህርት ቤቶች የተማሪዎች ዩኒፎርም /የደንብ ልብስ የጨርቅ ዓይነት፤ ጥራት እና ቀለም በትምህርት ቤቱ አስተዳደር፤ ተማሪዎችና ወላጆች የጋራ ስብሰባ በውይይት የተወሰነውን መጠቀም፣
- የወንድ ተማሪዎች የደንብ ልብስ አዘገጃጀት የሱሪ ቬል ስፋት ኖርማል ወይም ከ 18 ኢንች ያላነሰ ሲሆን ይንን መተግበር፣
- የሴት ተማሪዎች የደንብ ልብስ አዘገጃጀት የቀሚስ መጠን ከጉልበት በታች ያለውን 2/3ኛ የእግር ክፍል የሚሸፍን መሆን ስላለበት ይህንን መጠበቅ፣
- ማንኛውም ተማሪ ከተወሰነው የደንብ ልብስ ዓይነት፤ ጥራትና ቀለም ውጪ አለመጠቀም ፣ ከት/ቤቱ ህጋዊ ፈቃድ ውጪ ማንኛውንም ዓይነት የአርማ ፅሁፍ አለማሳተም፤
- ሌላ የጨርቅ ዓይነት ቀጥሎ አለማሰፋት እና ያልተፈቀደ የደንብ ልብስ ዓይነት፤ ቅርፅና ይዘት አለመጠቀም፣

# የቀጠለ

- የተማሪዎች ዩኒፎርምን በተመለከተ የማታ እና የርቀት ተማሪዎችን አይመለከትም፤
- የፀጉርን ንፅህና መጠበቅ፣
- ማንኛውንም አይነት የፀጉር ቀለም አለመቀባት፤
- ወንድ ተማሪዎች ፀጉራቸውን አንጨብሮ አለማሳደግ፤
- ሴት ተማሪዎች ፀጉራቸውን ባግባቡ ማበጠርና ማስያዝ፤
- ለሴት ተማሪዎች ተንጠልጣይ የጆሮ ተንጠልጣይ ጉትቻ አለማድረግ፤ እና
- ከጆሮ ውጭ የትኛውም የሰውነት አካል ላይ ለማጌጥ ተብሎ አለማስበሳትና ጌጦችን አለማድረግ፤
- ወንድ ተማሪ የጆሮ ጌጥ አለማድረግ፤
- እነዚህ ከላይ የተገለፁትን ግዴታዎች የማያከብር ቀላል የዲሲፐሊን ቅጣት ይወሰንበታል።
- በትምህርት ቤት ውስጥ የስርቆት ድርጊት ፈጽሞ አለመገኘት፣
- ሴት ተማሪዎችን አለመተንኮስ፣ አለማስፈራራት፣
- ቁማር አለመጫወት እና ከመሳሰሉ ሕገወጥ ድርጊቶችና ጥፋቶች መራቅ፣
- ሲጋራ አለማጨስ፣ የአልኮል መጠጥ ጠጥቶ አለመገኘት፣ ሺሻ አለመጠቀም፣ ጫት አለመቃም፣ ሌሎች አደንዛዥ ዕፆችን አለመጠቀም፣
- ት/ቤቱና ወላጅ ባላወቁት እና አሳማኝ ባልሆኑ ምክንያቶች ከት/ቤት አለመቅረት፣ አሳማኝ በሆኑ ምክንያቶች በአመቱ የትምህርት ካላንደር ከ10% እስከ 20% በላይ አለመቅረት፤

# የቀጠለ

- የት/ቤቱን ንብረት ሆንብሎ አለመስበር፣ አለማበላሸትና አለማጥፋት፣
- በፈተና ወቅት ሁከት አለመፍጠር፣ የፈተና ሰርዓቱ እንዲደናቀፍ አለማድረግ፣ አለመኮረጅና አለማስኮረጅ፣
- የት/ቤቱን መምህራን፤ ሠራተኞችና ኃላፊዎችን አለመሳደብና አለማንጓጠጥ እና ለመደብደብ አለመሞከር፤
- ተማሪዎችን አለመደብደብ፣ ንብረት አለመንጠቅ አለማስፈራራት፣
- እነዚህ ከላይ የገለጽናቸውን ግዴታዎች ያለመወጣት እስከ 1ዓመት ከትምህርት ቤት የማሰናበት ከባድ ቅጣት የሚያስቀጡ ናቸው።
- አደገኛ የሆኑ ስለታማ እና የጦር መሳሪያዎችን በት/ቤት ቅጥር ግቢ ይዞ አለመገኘት፣
- በፈተና ወቅት ስልክ፣ ታብሌት ይዞ አለመምጣት፤
- በፈተና ወቅት የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች አለመጠቀም፣ ተገቢ ያልሆነ ተግባር አለማከናወን፤ (ተማሪ የሚያወናብዱ መረጃዎች አለማስተላለፍ፤ ወዘተ)
- ሴት ተማሪዎችን አለመደባደብና ሰብአዊ መብታቸውን አለመጣስ፣
- ማንኛውም ጾታዊ ወይም ወሲባዊ ግንኙነት አለመፈጸም፣
- ትምህርት ሴኩላር በመሆኑ በት/ቤት ግቢ ውስጥ ሀይማኖታዊና ፖለቲካ እንቅስቃሴዎችን አለማካሄድ፣

# የቀጠለ

- በማንኛውም የቡድን ጸብ እና አምባጓሮ ተግባር ላይ አለመሳተፍ ፣
- ከኢትዮጵያዊ እሴቶች ያፈነገጡ እና ህጋዊ ያልሆኑ ድርጊቶችን እና በዓላትን አለማክበር እና አለመፈጸም ለምሳሌ /ዋተርዴይ፤ክሬዚ ዴይ፤ እራቁት ቀን ከለር ዴይ ወዘተ.../
- በት/ቤቱ ግቢ ውስጥ ማንኛውንም በአካልና በጤና ላይ ጉዳት የሚያደርስ የጦር መሳሪያ ይዞ አለመገኘት፣
- የት/ቤቱን ንብረት ሆን ብሎ ለጉዳት አለማጋለጠ፣
- በፈተና ወቅት ለሌላ ተማሪ አለመፈተን ወይም ለራስ አለማስፈተን፣
- የተጭበረበረ የትምህርት ማስረጃ አለማቅረብ፣
- መምህራንና የትምህርት ቤቱን ሠራተኞች አለመደባደብ፣
- የአንድ ዓመት ከትምህርት ቤት የመታገድ ቅጣት ተፈጻሚ የሆነበት ተማሪ በድጋሚ ጥፋት ፈጽሞ አለመገኘት፣
- እነዚህ ከላይ የተገለፁት ግዴታዎችን ተላልፎ መገኘት እስከ መጨረሻው ከትምህርት ቤት መታገድን ጨምሮ በመደበኛው ፍርድ ቤት በህግ የሚያስጠይቅ መሆኑ መታወቅ አለበት።

# መመሪያውን አክብረው ግዴታቸውን የማይወጡ ተማሪዎች ላይ የሚወሰድ የዲሲፕሊን ቅጣቶች

| ቀላል የዲሲፕሊን ቅጣቶች | | ከባድ የዲሲፕሊን ቅጣቶች | | |
|---|---|---|---|---|
| የቃል ማስጠንቀቂያ . | የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ | ለአንድ ዓመት ከትምህርት ቤት ማገድ፣ | ከትምህርት ቤት ማሰናበት | በመደበኛው የህግ ሥርዓት መዳኘት |

አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ
BIIROO BARNOOTA BULCHINSA MAGAALAA FINFINNEE
ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION EDUCATION BUREAU

# ክፍል አራት

## 4. ቀጣይ ፈተናዎችና የምንሻገርባቸው አቅጣጫዎች

- በሃገራችን ለነበረው የፖለቲካ ስርአት የጣለው ጠባሳ እንዲህ በቶሎ የሚቀየር አይደለም በመሆኑም አሁንም ፀረ-ህዝብ ሃይሎች እጃቸውን ከትምህርት ስርአቱ ላይ እንዲህ በቀላሉ አያነሱም።
- ሌላው ቀጣይ ፈተናችን ጥቂት ስነምግባር የጎደላቸውን ተማሪዎች በአጭር ጊዜ ውስጥ ከችግራቸው ተላቀው ወደ ስርአት ስለማይገቡ ሌሎች ጤናማ ተማሪዎችን በማደናገር በጎ ያልሆነ የአቻ ግፊት መፍጠራቸው የማይቀር በመሆኑ በተማሪዎች መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ያለምንም ማወላወል የዲሲፕሊን እርምጃ እየወሰዱ መሄድ ያስፈልጋል።



fppt.com

# የቀጠለ

- አሁንም በብሄር ጽንፈኝነት፣ በሃይማኖት አክራሪነት፣ ትምህርት ቤትንና ተማሪዎችን ከመፈተን አይቦዝኑም በመሆኑም እንደከዚህ ቀደሙ ሁሉ ተማሪዎች ከወላጆች መምህራንና የትምህርት አመራሮች ጋር በመተባበር ልንመክተው ይገባል፡



fppt.com

# የቀጠለ

- ሁለተኛው የትኩረት ነጥብ፡- የትምህርት ውስጣዊ ብቃትን ማሳደግ ነው በዚህም ወደ ትምህር ቤት የገቡ ተማሪዎች ትምህርት እንዳያቋርጡ፣ ክፍል እንዳይደግሙ፣ እንዳይቀሩ እንዳያረፍዱ የሚሰራበት ነው በዚህ ስራ አብዛኛውን የሚመለከታቸው ወላጆች ናቸው።
- በመሆኑም በድጋፍና ክትትል ስራችን እናዳረጋገጥነው ጥቂት የማይባሉ ተማሪዎች በተለይም 2ኛ ደረጃ እና 8ኛ ክፍል ላይ የማርፈድ፣ የመቅረትና የማቋረጥ ክፍተቶች ከፍተኛ ችግሮች ናቸው።



fppt.com




## በእዉቀት፤በክህሎትና በስነምግባር የታነጸ ትዉልድ ለሀገር ግንባታና እድገት  መሰረት ነዉ!!!!

## አመሰግናለው